ሠላሳ ስምንተኛ ዓመት ቊጥር ፱
38th Year — No. 9

አዲስ አበባ ግንቦት ፲ ቀን ፲፱፻፸፩ ዓ. ም.
Addis Ababa, 18th May, 1979

የኢትዮጵያ ጊዜያዊ ወታደራዊ መንግሥት

ነጋሪት ፡ ጋዜጣ ።
NEGARIT GAZETA

የአንዱ ዋጋ ብር 0.55

በጊዜያዊ ወታደራዊ አስተዳደር ደርግ
የሚኒስትሮች ምክር ቤት ሰብሳቢ
ጽሕፈት ቤት ተጠባባቂነት የወጣ

የፖስታ ሣጥን ቊጥር ፩ሺ፴፩ (1031)

ማውጫ
፲፱፻፸፩ ዓ. ም.

አዋጅ ቊጥር ፩፻፷፩/፲፱፻፸፩ ዓ. ም.
የከተማ ቦታ ኪራይና የከተማ ቤት ግብር
(ማሻሻያ) አዋጅ . . . . ገጽ ፩፻፭

የሕግ ክፍል ማስታወቂያ ቊጥር ፷፬/፲፱፻፸፩ ዓ. ም.
የክፍላተ ሀገር ከተሞች ቦታ ኪራይና
የከተማ ቤት ግብር ደንብ . . . . ገጽ ፩፻፯

CONTENTS
1979

Proclamation No. 161 of 1979
Urban Land Rent and Urban Houses Tax
(Amendment) Proclamation .... Page 105

Legal Notice No. 64 of 1979
Provincial Urban Land Rent and
Urban House Tax Regulations .. .. Page 107

አዋጅ ቊጥር ፩፻፷፩/፲፱፻፸፩ ዓ. ም.
የከተማ ቦታ ኪራይና የከተማ ቤት ግብር አዋጅን ለማሻሻል የወጣ አዋጅ

«ኢትዮጵያ ትቅደም»

የጊዜያዊ ወታደራዊ አስተዳደር ደርግንና የሚኒስትሮች ምክር ቤትን ሥልጣንና ኃላፊነት እንደገና ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር ፩፻፲/፲፱፻፷፱ ዓ. ም. አንቀጽ ፭/፮/መሠረት የሚከተለው ታውጅዋል ።

፩ ፤ አጭር ርእስ ፤

ይህ አዋጅ «የከተማ ቦታ ኪራይና የከተማ ቤት ግብር (ማሻሻያ) አዋጅ ቊጥር ፩፻፷፩/፲፱፻፸፩ ዓ. ም.» ተብሎ ሊጠቀስ ይቻላል ።

፪ ፤ ማሻሻያ

የከተማ ቦታ ኪራይና የከተማ ቤት ግብር አዋጅ ቊጥር ፹/፲፱፻፷፰ ዓ. ም. እንደሚከተለው ተሻሽሏል ፤

፩/ የአንቀጽ ፮ ንዑስ አንቀጽ ፩ ተሽሮ በሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀጽ ፩ ተተክቷል ፤
«፩/ ኪራይ ከዚህ ጋር ተያይዞ በሚገኘው ሠንጠረዥ እንደተመለከተው በቦታው ደረጃ ላይ የተመሠረተ ይሆናል ። »

፪/ የአንቀጽ ፲፱ ንዑስ አንቀጽ ፩ ተሽሮ በሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀጽ ፩ ተተክቷል ፤
«፩. ይህን አዋጅ ለማስፈጸም የከተማ ልማትና ቤት ሚኒስትር ደንብ ለማውጣት ይችላል ። »

፫/ ከአዋጅ ቊጥር ፹/፲፱፻፷፰ ዓ. ም. ጋር ተያይዞ የሚገኘው ሠንጠረዥ ፪ ተሽሮ በሚከተለው አዲስ ሠንጠረዥ ፪ ተተክቷል ፤

PROCLAMATION No. 161 OF 1979
URBAN LAND RENT AND URBAN HOUSES TAX AMENDMENT PROCLAMATION

"ETHIOPIA TIKDEM"

In accordance with Article 5(6) of the Redefinition of Powers and Responsibilities of the Provisional Military Administrative Council and the Council of Ministers Proclamation No. 110/1977 it is hereby proclaimed as follows:

Habesha Legal Advocates LLP

1. *Short Title*

This Proclamation may be cited as the "Urban Land Rent and Urban Houses Tax (Amendment) Proclamation No. 161/1979".

2. *Amendment*

The Urban Land Rent and Urban Houses Tax Proclamation No. 80/1976 is hereby amended as follows:

1/ Sub-article 1 of Article 6 is deleted and replaced by the following new sub-article 1:
"1/ Rent shall be based on the grade of the land as indicated in the Schedule hereto."

2/ Sub-article 1 of Article 19 is deleted and replaced by the following new sub-article 1:
"1/ The Minister of Urban Development and Housing may issue regulations necessary for the better carrying out of this Proclamation."

3. Schedule 2 that is attached to Proclamation No. 80/1979 is deleted and replaced by the following new schedule 2:

ሠንጠረዥ ፪

ለመሥሪያ ቤት የተያዘ ቦታ ኪራይ ተመን

ሠንጠረዥ

የቦታ መጠን	በ፩ኛ ደረጃ የተመደበ ቦታ ኪራይ መጠን ሜትር ካሬው በብር ሂሣብ		በ፪ኛ ደረጃ የተመደበ ቦታ ኪራይ መጠን ሜትር ካሬው በብር ሂሣብ		በ፫ኛ ደረጃ የተመደበ ቦታ ኪራይ መጠን ሜትር ካሬው በብር ሂሣብ	
	ንዑስ ደረጃ ፩ ለአገልግሎትና ለኢንዱስትሪ	ንዑስ ደረጃ ፪ ለእርሻና ከብት እርባታ	ንዑስ ደረጃ ፩ ለአገልግሎትና ለኢንዱስትሪ	ንዑስ ደረጃ ፪ ለእርሻና ከብት እርባታ	ንዑስ ደረጃ ፩ ለአገልግሎትና ለኢንዱስትሪ	ንዑስ ደረጃ ፪ ለእርሻና ከብት እርባታ
በያንዳንዱ ሜትር ካሬ	እስከ 0.06	እስከ 0.04	እስከ0.04	እስከ 0.03	እስከ 0.02	እስከ 0.003

SCHEDULE 2

SCHEDULE SHOWING RATE OF RENT PAYABLE ON URBAN LAND USED FOR BUSINESS HOUSES

Area of Land	Rate of Rent on Land in Grade 1 in Birr per Sq. Meter		Rate of Rent on Land in Grade 2 in Birr per Sq. Meter		Rate of Rent on Land in Grade 3 in Birr per Sq. Meter	
	Sub-Grade 1 Service & Industry	Sub-Grade 2 Agriculture	Sub-Grade 1 Service & Industry	Sub-Grade 2 Agriculture	Sub-Grade 1 Service & Industry	Sub-Grade 2 Agriculture
Per Square Meter	up to 0.06	up to 0.04	up to 0.04	up to 0.03	up to 0.02	up to 0.003

Habesha Legal Advocates LLP

፫፡ አዋጁ የሚጸናበት ጊዜ፤

ይህ አዋጅ ከነሐሴ ፫ ቀን ፲፱፻፷፯ ዓ. ም. ጀምሮ የጸና ይሆናል ።

አዲስ አበባ ግንቦት ፲ ቀን ፲፱፻፸፩ ዓ. ም.

ጊዜያዊ ወታደራዊ አስተዳደር ደርግ

3. *Effective Date*

This Proclamation shall enter into force as of the 9th day of August 1975.

Done at Addis Ababa, this 18th day of May, 1979

THE PROVISIONAL MILITARY ADMINISTRATIVE COUNCIL

* * * * * *